

አጭር ማብራሪያ

# የሴቶች ሠላምና ፀጥታ አጀንዳ፡ በኢትዮጵያ በሠላምና ግጭት አፈታት የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ

ፎቶ: ዩኤን ውመን / ካትያን ቲጄሪና

## ዳራ እና አጠቃላይ ሁኔታ

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ክፍል የኢትዮጵያ ቢሮ (ዩኤን ውመን) ሴቶች ሠላምና ደህንነት በሚል ርዕስ ሕዳር 23 እና 24 2013 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሴቶች በሠላም እና በግጭት አፈታት ያላቸውን ተሳትፎ ስለማሳደግ የመከረ አውደጥናት አዘጋጅቶ ነበር። የአውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳን በተመለከተ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የመንግስት አካላት ግንዛቤያቸውን እንዲጨምሩ ለማድረግና እነዚሁ አካላት በተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት የወጣው 1325 ውሳኔን ተመርኩዘው የብሄራዊ መርሀ ግብርን ማውጣት አስፈላጊነትን እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። በዚህ መሠረት ዩኤን ውመን አጀንዳው በኢትዮጲያ እንዲተገበር ባለው ቁርጠኝነት በሚያደርገው ድጋፍ በአውደጥናቱ በቀረቡ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችና በተደረጉ ውይይቶች ላይ ተመርኩዘው የተሰጡ የውሳኔ ሃሳቦችና ቁልፍ ግኝቶችን መሠረት ያደረገ ይህ አጭር የፖሊሲ መግለጫ ተዘጋጅቷል። እንደ ዩኤን ወመን እምነት በአቅራቢዎችና በተወያዮች የቀረቡት የውሳኔ ሀሳቦች እና ግኝቶች ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ብሄራዊ የድርጊት መርሀ ግብሩን ለማውጣት ጠቃሚ ግባቶች ይሆኗቸዋል፤ በተለይም የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1325ን ተመርኩዞ ብሄራዊ የድርጊት መርሃግብሩን ለማውጣት በወሳኝ የዝግጅት ሂደት ላይ ለሚገኘው የኢትዮጵያ መንግስት ያግዙታል።

አውደጥናቱ በዩኤን ውመን እና በሌሎች ባለሙያዎች አማካይነት ጥናታዊ ጽሁፎች የቀረቡበትና ማዳበሪያ ሃሳቦች የተስተናገዱበት፤ እንዲሁም በተሳታፊዎች መካከል ውይይት እንዲካሄድ የተመቻቸበት መድረክ ነበር። ዩኤን ውመን ስለ የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳ ምንነትና ዓለም አቀፍ ማዕቀፉን፡ የተ.መ.ድ ፀጥታ ምክር ቤት ከ1992 እስከ 2011 ዓ.ም. (እ.አ.አ ከ2000 እስከ 2019) ድረስ ያወጣቸውን 10 የውሳኔ ሃሳቦች፤ አጀንዳው የሚያጠቃልላቸውን ዋና ክፍሎች ማለትም አራቱ ስልታዊ ምሶሶዎች፡ መከላከል፣ ጥበቃ ማድረግ፣ ተሳትፎ እንዲሁም እፎይታና ማገገምን በተመለከተ አቅርቧል። የሴቶች ሠላምና እና ደህንነት ብሄራዊ የድርጊት መርሀ ግብርን ተግባራዊ ማድረግ ስለሚኖረው ጠቀሜታና እንዲሁም የመርሀግብሩ ሂደት ደረጃ በደረጃ ክንውኖችም በዩኤን ውመን የጥናት ጽሁፍ ተካቷል። በተጨማሪም የአገሪቱ የተለያዩ አካላት በሴቶች ሠላም እና ደህንነት ጉዳይ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ አስመልክቶ በቅርቡ ስለተደረገው ጥናት አጠቃላይ ውጤት በዩኤን ውመን ገለጻ ተደርጓል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ባለድርሻ አካላት ያላቸው ግንዛቤ፣ እውቀትና ተሳትፎ አነስተኛ ነው። ስለሆነም የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ጠንካራ መሆኑን ለማረጋገጥ የአቅም ግንባታ፣ የተሻለ ቅንጅት፣ የተሞክሮ መለዋወጥ እና የግንኙነት መረብ መዘርጋት ያስፈልጋል።

ስለአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ፣ ሕግ አውጪው እና ፖሊሲ እንዲሁም ስለወደፊቱ ተግባራዊ ፍላጎቶች በመረጃ የተረጋገጠ መረጃ ለመለዋወጥና ለመወያየት የሚያስችሉ አራት የአካዳሚክ እና የውይይት የጥናት ወረቀቶችም ቀርበው ነበር። **እንጉዳይ መስቀል** የተባሉ አቅራቢ ‹‹በትጥቅ ግጭት እና መፈናቀል ሳቢያ በድብቁ ዓለም ውስጥ ያሉ ሴቶች ሁኔታ በጨረፍታ፤ የፆታ ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሕጎች ትንታኔ›› በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበዋል። ጽሁፉ የኢትዮጵያ ሕጎች ከግጭቶች ጋር በተያያዘ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ወሲባዊ ጥቃት እስከምን ድረስ መከላከል እንደሚችሉ ይተነትናል። ‹‹በግጭት ቀጠናዎች ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን መከላከል፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ሴቶች ተኮር የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ጥሪ›› በሚል ርዕስ የጥናት ጽሁፍ ያቀረቡት ደግሞ **ሙሉጌታ ተስፋዬ ተሾመ** ነበሩ። ጥናቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭትን ተከትሎ በአማራ ክልል የደረሱ ፆታ ላይ የተመሠረቱ ጥቃቶች መጠንን እና በአካባቢው የተደረገው መልሶ የማቋቋም ፕሮግራም ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ ስለመሆኑ የዳሰሰ ሲሆን ወደፊትም የሚከናወኑ የድጋፍ እና ማቋቋሚያ ፕሮግራሞች ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው።

ሌላው ጽሁፍ አቅራቢ **ያዕቆብ ጥላሁን ይመር** ‹‹የተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) አባላት የሴቶች ሠላም እና የደህንነት አጀንዳን ስለመደገፍ ያላቸው ግንዛቤ›› በሚል ርዕስ የምክር ቤት አባላቱ

ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ ሕግ በማውጣት፣ በክትትልና በጀት በመመደብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ቁልፍ አካላት እንደሆኑም ተንትነዋል፡፡ በመጨረሻም ‹‹የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳን በመደገፍና አውድ በመፍጠር ዋጋ ያልተሰጠው የሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾች ሚና በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ **በውብርስት ፋንታሁን** የተዘጋጀው ጥናት ቀርቧል፡፡ በኢትዮጵያ ሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾች ለአጀንዳውተግባራዊነት ስለሚኖራቸው ሚና እና አስተዋጽኦ፤ ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮችና ሴት የመብት ተሟጋቾቹን ደህንነት ለማስጠበቅ ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎችን ተግባራዊ ስለማድረግ አስፈላጊነት በጥናቱ ተብራርቷል፡፡

## ቁልፍ ግኝቶችና የውሳኔ ሃሳቦች

### አጠቃላይ የውሳኔ ሃሳቦች

• የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1325ን (1992 ዓ.ም.) በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ማጽደቅ፤ ለኢትዮጵያ የሠላም ግንባታ ጠቀሜታነት ሲባል የሚዘጋጀው መርሃ ግብር በሥራ ላይ የሚገኙ ጠቃሚ እቅዶችን፣ ፖሊሲዎች፣ የሕግ ማዕቀፎችና ስልቶችን ሊያካትት ይገባል፡፡ የሚነደፈው የድርጊት መርሀ ግብር አራቱን የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳ ምሰሶዎችንም በሙሉ ሊያካትትና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በስፋት በጋራ ሊመክሩበት፤ ለተግባራዊነቱ በቂ በጀት ሊመደብለት ይገባል፡፡

• ሴቶች በሠላም ግንባታ፣ ግጭትን በመከላከልና በመፍታት እንዲሁም በፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ የሚኖራቸው የጠነከረ ተሳትፎ እንዲጨምር እና ተቋማዊ እንዲሆን ማድረግ፤ ለዚህም አገር አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መደገፍ፤

### ሴቶችን ከግጭት ጋር ተያይዞ ከሚደርሱ ወሲባዊ የፆታ ጥቃቶች የሚከላከሉ የሕግ ማዕቀፎች

ግኝቶች

• ወሲባዊ ጥቃት በትጥቅ ግጭቶች ወቅት የሚፈጸም ዋነኛ የጥቃት ማሳያ ድርጊት ሲሆን በሰሜን ኢትዮጵያ ባለው ግጭት ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ሁሉ ወሲባዊ ጥቃት የመፈጸም ተግባር ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

• ኢትዮጵያ ወሲባዊ ጥቃትን እንደ አንድ የጦርነት ስልት መጠቀምን የሚከለክሉትን የሠብአዊ መብት እና የወንጀል ሕግን የያዘውን የዓለም አቀፍ የሠብአዊ መብት ሕግን ተቀብላለች፡፡ ይሁንና የኢትዮጵያ ብሄራዊ መደበኛ የሕግ ማዕቀፍ ከግጭት ጋር የተገናኙ ወሲባዊ ጥቃቶችን በተመለከተ የሚሰጠው በቂ ጥበቃና ተመጣጣኝ ቅጣት የለውም፡፡ እንደውም ጥቃት አድራሾቹ ያለምንም ቅጣት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል፡፡

• የኢትዮጵያ ሠብአዊ መብት ኮሚሽንና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ግጭትን ተከትሎ የሚደርሱ ወሲባዊ ጥቃቶችን ለማስቆም የሠብአዊ መብቶች ክትትል በማድረግና የሕግ ማዕቀፉ እንዲጠናከር በመቀስቀስ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡

የመፍትሄ ሃሳቦች

• ለዓለም አቀፍ የጦር ወንጀሎች እና በሠው ልጆች ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች በቂ ሽፋን ለመስጠት ያስችል ዘንድ የወንጀል ሕጉን ጨምሮ ሌሎች ብሄራዊ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉ ማድረግ፤ ሴቶችን ከግጭት ጋር ተያይዞ ከሚደርሱ ወሲባዊና ሌሎች ፆታን መሠረት ካደረጉ ጥቃቶች ለመከላከልና አጥፊዎችንም ተጠያቂ ለማድረግ የመንግስትን ተቋማዊ አቅም ማሳደግ፤

• በግጭት ውስጥ ሴቶችን ከወሲባዊ እና ሌሎች ፆታን መሠረት ካደረጉ ጥቃቶች ለመከላከል እንዲያስችል፣ የመካስና የመዳኘት መብታቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ የሠብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራዎችን ማከናወን፤

### በአማራ ክልል በግጭት ወቅት የደረሱ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች

ግኝቶች

• በአማራ ክልል ግጭት በነበሩባቸው አካባቢዎች ፆታን መሠረት ያደረጉ ወሲባዊ፣ የአካል እና የሥነልቡና ጥቃቶች በስፋት አጋጥመዋል፡፡ በተጨማሪም የአካል ጉዳቱ ሴቶችና ልጃገረዶችን በሥነልቡና ስብራትና በአኮኖሚ ችግር እንዲሰቃዩ እያደረጋቸው ነው፡፡

• በአማራ ክልል ግጭቶች በተስፋፉባቸው አካባቢዎች ሴቶችን ፆታን መሠረት ካደረጉ ጥቃቶች ለመከላከል የተደረገው ጥረት አነስተኛና ለደረሰባቸው ጥቃትም በሕግ የሚካሱበት መንገድ የለም፡፡

• በተጨማሪም በክልሉ የሚገኙ መጠለያዎችና የአካባቢው ተፈናቃይ መኖሪያ ካምፖች የተጨናነቁና በቂ የውሃ አቅርቦት፣ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት፣ የሥነተዋልዶ ጤናን ጨምሮ የጤናና የማህበራዊ አገልግሎቶች እጦት አለባቸው፡፡ በውጤቱም ከቀያቸው የተፈናቀሉት ሴቶችና ልጃገረዶች ለአካል ደህንነት ስጋት፣ ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃትና ከፍተኛ ለሆነ ወሲባዊ ብዝበዛ የተጋለጡ ናቸው፡፡

የመፍትሄ ሃሳቦች

• በአማራ ክልልና በአጠቃላይ የአገሪቱ ሴቶችን ፆታን/ግጭትን መሠረተ ካደረጉ ወሲባዊ ጥቃቶች ለመከላከልና ጥቃት ለደረሰባቸውም ሁሉን አቀፍና ጥራቱ የተሟላ አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኙ ማረጋገጥ የሚያስችል ውጤታማ ዘዴዎችን መዘርጋት፤

UN WOMEN

- ድህረ ግጭት መልሶ የማገገሚያ/ማቋቋሚያ እቅዶች ሴቶች በሠላም ግንባታ፣ በግጭት አፈታት እና በኤኮኖሚ መልሶ ግንባታ ውስጥ ያላቸውን ውጤታማ ተሳትፎ በደንብ የሚያሳድጉና የሚደግፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ የሴቶች ፍላጎቶች፣ ያገባኛል ባይነትና የተለወጡ እውነታዎችን በምጣኔ ሀብት እቅዶች፣ ታጣቂዎችን ወደ ሠላማዊ ሕይወት በመመለስ፣ ትጥቅ በማስፈታት እና መልሶ በማቀላቀል ተግባራት ውስጥ ማካተት፤

- ሴቶች በግጭት አፈታት ዘዴዎች ውስጥ የሚኖራቸውን ጉልህ ሚና እና አስተዋጽኦ መገምገም እንዲሁም መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የሠላም ሂደቶች ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፏቸውና አስተዋጽዋቸውን መለየት፤

## የፓርላማ አባላት ስለ ሴቶች፣ ሠላምና ደህንነት አጀንዳ

### ግኝቶች

- በ2013 በተደረገው ስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ የተመረጡ የፓርላማ አባላት ስለ ሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳ በተመለከተ ስላላቸው ዕውቀት በተደረገ ጥናት መጠነኛ ዕውቀት እንዳላቸው ሲታወቅ ይህንኑ በዘላቂ ልማት ግቦች ትልቅ አውድና በብሄራዊ የልማት ግቦች ውስጥ ማስቀመጥ ይችላሉ። ነገር ግን የሴቶች ሠላም እና ደህንነት አጀንዳን እውን ለማድረግ የችሎታ ደረጃቸውን በራሳቸው በመገምገም ረገድ ከፍተኛ ልዩነት አለ።

- በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የፓርላማ አባላት የሴቶች ሠላምና ደህነት አጀንዳን መሠረታዊ ነገሮች እና አጀንዳውን ለመመስረት መነሻ የሆኑ የውሳኔ ሃሳቦችን፣ የአጀንዳውን ምሰሶዎችና የብሄራዊ የድርጊት መርሀግብር ሚናን ጭምር አስመልክቶ ጥልቅ የሆነ የግንዛቤ አቅም ያንሳቸዋል። ይሁንና አጀንዳውን ተግባራዊ ለማድረግ ፓርላማው ስለሚኖረው ሚናና ስለአጀንዳው ቀና አመለካከት እያሳዩ ነው።

### የመፍትሄ ሃሳቦች

- የተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳን እና ሌሎች ተያያዥ የሕግ ማዕቀፎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሕግ በማውጣት፣ በመከታተልና በጀት በመመደብ ወሳኝ ሚና ያለው ቁልፍ አካል ነው። ስለሆነም በአጀንዳውና በተወካዮች ምክር ቤት ሚና ላይ ያተከሩና የምክር ቤቱ አባላትን ዒላማ ያደረጉ ስልጠናዎችን ፤ የውይይት እና የግንዛቤ መስጫ መድረኮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

- በኢትዮጵያ የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳን በቁርጠኝነት ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎች የመንግስት ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ከምክር ቤቱ ጋር አብረው ሊሠሩ ይገባል።

## የሴቶች ሠላምና ደህንነት አጀንዳን በመደገፍ ሴት የሠብአዊ መብቶች ተሟጋቾች የሚኖራቸው ሚናና የሚያጋጥሟቸው ችግሮች

### ግኝቶች

- ሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾች ግጭቶች ከመፈጠራቸው በፊት፣ በተፈጠሩ ጊዜና ከተፈጠሩ በኋላ ባሉ ሁኔታዎች የሠብአዊ መብቶችንና ዘላቂ ሠላምን በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ሚና አላቸው። ተሟጋቾቹ ግጭቶቹ በሚገኙባቸው ግንባሮች እና በታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ደረጃ በመገኘት እርዳታ መስጠት፣ ለሠላማዊና ሁሉን አካታች ስለሆነ የግጭት አፈታት ዘዴ ማስተማር እና ተከታታይ የክትትል ተግባር ይሠራሉ።

- ሴት የሠብአዊ መብቶች ተሟጋቾችን ለመከላከልና ለመደገፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ በወጡት ድንጋጌዎች፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ አድላዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የተደረገው ሥምምነት ድንጋጌ፣ በቤጂንግ መግለጫና የድርጊት መርሀግብር፣ በተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔና በሠብአዊ እና በህዝብ መብቶች የአፍሪካ ኮሚሽን ውሳኔ ላይ ተረጋግጧል።

- ሁሉም የሠብአዊ መብት ተሟጋቾች ከሚያጋጥሟቸው ተመሣሣይ ስጋቶችና የሠብአዊ መብት ጥሰቶች በተጨማሪ በሠላምና በግጭት አፈታት ላይ የሚሠሩ ሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾች ወሲባዊና ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በቤት ውስጥ፣ በአደባባይ እና በኢንተርኔት መስመሮች ያጋጥሟቸዋል። የደህንነት ጥበቃ አለመኖር፣ ፍትህ እና ወቅታዊና ትክክለኛ የፍርድ አሰጣጥ አለማግኘታቸው ስጋቶቻቸውን ከፍ ያደርገዋል። ከሁሉም በላይ በኢንተርኔት የሚሰነዘር የወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት ማስፈራሪያ ሙሉ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ተጨማሪ ችግር የሚፈጥርባቸው ሲሆን በሕግ ማዕቀፍ በበቂ ሁኔታ ምላሽ አይሰጡም/ትኩረት አያገኙም።

### የመፍትሄ ሃሳቦች

- ሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾችን ለመከላከል የወጡ ዓለም አቀፍ ቃልኪዳኖች ሀገራዊ ቅርጽ እንዲይዙ ማድረግና ያሉትን የሕግ ማዕቀፎች በመገምገምና የሴት ተሟጋቾቹን የጥበቃና የተሳትፎ መብት የሚያረጋግጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ መከለስ፤

- በኢትዮጵያ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ውስጥ ሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾችን ሚናና ተሳትፎ መገምገምና በግጭት አፈታት እና የሠላም ግንባታ ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ በማህበራዊ ተቋማትና በሥነስርዓት ሁነቶች አማካይነት በታችኛው የእርከን ደረጃ ማሳደግ፤

- የሴት የሠብአዊ መብት ተሟጋቾችን ደህንነት ለማረጋገጥና በሠላም ግንባታና በግጭት አፈታት የመሥራት ዕድላቸውን እንዲሁም ስለሚናቸውና መብታቸው የግንዛቤ ማስጨበጫን ጨምሮ ተጨባጭ እርምጃ መውሰድ፤ በተጨማሪም በሴት ተሟጋቾቹ ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተደራጀ ሁኔታ መሠነድና ወቅታዊ የሆነ የመከላከል እርምጃ ማከናወን፤

ማስተባበያ

ናቸው እንጂ የግድ የተባበሩት መንግስታት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃት ክፍል (የዩኤን ውመን)፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ወይም ማንኛውንም ተዛማጅ ድርጅቶችን አስተያየት አይወክልም።
የዚህ ሕትመት ይዘት በተጨባጭ ትክክለኛና በትክክል የተጠቀሰ መሆኑን ለማረጋገጥ ምክንያታዊ ጥረቶች ሲደረጉም፣ የዩኤን ውመን  የዚህን ጽሑፍ ይዘት በመጠቀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች ወይም ጉዳቶች ኃላፊነቱን አይወስድም። ሰነድ፣ ከእንግሊዝኛ ውጪ ወደ ቋንቋዎች መተርጎምን ጨምሮ።

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።